ያ ትውልድ

የ«ያ ትውልድ ተቋም» ልሳን

ያ ትውልድ ቅጽ 4 ቁጥር 1 የካቲት ፲፮ ቀን ፪ ሺህ ፱ ዓ.ም.

# የካቲት 66 መሪ ኮከቡን ያጣ አብዮት

*(የካቲት 66 ሕዝባዊ አብዮት 43ኛ ዓመት ምክንያት በማድረግ)*

ኢትዮጵያ ሀገራችን ታዳጊ ሀገሮችን በተለይ አፍሪካን እንደ ቅርጫ የተቀራመቱት ቅኝ ገዥዎችና ወራሪዎችን ጥቃት መክታ የግዛት አንድነቷንና ሉዓላዊነቷን መጠበቅ ብቻ ሳይሆን ለማንም ባዕዳን ወራሪ ኃይል ሳትደፈርና ሳትገዛ የኖረች የማንነታችንና የክብራችን መግለጫ ናት። ዮሐንስ በመተማ፣ ቴዎድሮስ በመቅደላ፣ ምኒልክ በአድዋ እየተባለ የሚነገርላቸው፣ የሚጻፍላቸው፡ የሚዘፈንላቸው ነገስታቶች በሀገር አንድነትና በኢትዮጵያዊነት ማንነት ወራሪን ያሳፈሩና ዓለምን ያስደነቁ ኢትዮጵያዊነት የክብርና የአንድነት ተምሳሌትነቷን ያስፃፉና ያስተረኩ እስከዛሬም ሆነ ወደፊት ይህ ማንነታቸውን ታሪክ የሚያወሳላቸው ነገስታት ናቸው።

በነዚህ ነገስታቶች የአገዛዝ ዘመን የሀገር አንድነትንና የግዛት ነፃነትን በማስከበር ደረጃ በየጊዜው ስማቸው የሚጠራ ጀግኖችን ሀገራችን አስመዝግባለች። ዶጋሌ ሲነሳ አሉላ አባ ነጋ፡ መድፍ ሲነሳ ፊታውራሪ ገበየሁና ባልቻ አባ ነፍሶ፡ ስቅላት ሲታወስ በላይ ዘለቀ፡ ብልጠት ሲጠቀስ እቴጌ ጣይቱ፣ ሞኝነት ሲዜም ደጃዝማች አያሌው ብሩ፣ እምነት ለነፃነት አቡነ ጴጥሮስ መሰል ጊዜ ያበቀላቸው ጀግኖች በዝማሬው፣ በተረቱ፣፡ በግጥሙ፣ በተውኔቱ ሲታወሱ ኖረዋል።

ኢትዮጵያ የተበታተነ የዘመነ መሳፍንት አገዛዝ ታሪክ አስመዝግባ በአንድ ማዕከላዊ መንግሥት ሥር ትተዳደር ዘንድ የተደረገው ትግልና የእርስ በርስ ጦርነት እንደማንኛውም ዓለም የታሪኳ አንዱ ገጽታ ቢሆንም ከሦስት ሺህ ዘመን በላይ የሚወስደን ታሪካችን ከበርካታ ሀገራት ቀዳሚ ሥፍራን ያስይዛታል። የዚህ ታሪክ ተረካቢ ነገስታት በሀገር አንድነት ከጥያቄ ባይገቡም ኢትዮጵያን በልማትና ዕድገት ጎዳና በማራመድ ለቀጣይ ትውልድ አርኣያ የምትሆን ኢትዮጵያን አቅጣጫ ማስያዙና መሰረት መጣሉ ላይ ብዙ የሚቀራቸው ነበር። ኢትዮጵያ የተፈጥሮ ሀብቷን ለዕድገት፣ የልጆቿን ጀግንነት ለልማትና ብልጽግና ትጠቀምበት ዘንድ ለትውልድ መሠረት የሚጥል አገዛዝ ማግኘት ተስኗታል። ምኒልክ በአድዋ፣ የኢትዮጵያ አርበኞችና፣ ጀግኖች በፋሽስት ወረራ የተቀዳጁትን ድል ለሀገር ዕድገትና ልማት ለማዋል አልታደለችም።

የሀገርን ሉዓላዊነትና የግዛት አንድነቷን በጀግኖች ልጆቿ ተጋድሎ ያስከበረች ሀገራችን ለድንቁርና፡ ድህነት፣ በሽታ፣ ረሀብ ግን እጇን ሰጥታለች። ነፃነቷን ጠብቃ የኖረች አኩሪ ሀገር በተደጋጋሚ የረሀብ ምርኮኛ ሆናለች። መተማ የፈሰሰው የዮሐንስ ደም፣ መቅደላ የተዘረጋው የቴዎድሮስ አካል “የጀግና ሰው ክብሩ ዳር ድንበሩ” ቢያዘፍንም ልጆቿን ሊመግብ ተስኖታል። የምኒልክ ጀግንነት በአድዋ ቢጻፍ፣ ቢተረክ፣ ቢዘፈን፣ ቢገጠም “ዳቦ ለተራበን” ከማስጠየቅ አልተገታም።

የየካቲት 1966 ሕዝባዊ አብዮት ሲነሳ በኢትዮጵያ የትግል ታሪክ ቀዳሚውን ሚና የሚጫወተው ወጣት ትውልድና ተማሪ ሲታወስ ይኖራል። ትግሉ አቅጣጫ ስቶ፣ ጉልበተኛ ጠልፎት፣ የታሰበው ቀርቶ ያልተገመተው፣ የተፈለገው ቀርቶ ያልተጠበቀው ሲመጣ ወቀሳን ለመሸሽ "ተማሪ ያመጣው ጣጣ" እየተባለ ይነገርለታል። የካቲት 66 ረሃብ፣ ድህነት፣ በሽታ ያመጣው ጣጣ ነው። የየካቲት 66 ሕዝባዊ አብዮት የመብት መረገጥ፣ የብልሹ መሬት ስሪት አስተዳደር፣ የኑሮ ውድነት፣ የኋላ ቀር አስተዳደር ጣጣ የወለደው ነው።

መሬት አልባው አርሶ አደር የመሬቱ ባለቤት እንዲሆን ነው "መሬት ለአራሹ!" መሪ መፈክር የሆነው። የሰው ልጆች የዜግነት መብትን ጨምሮ የመደራጀት፣ መሰብሰብ፣ የመጻፍ፣ ሰላማዊ ሰልፍ የማድረግ መሰል ዴሞክራሲያዊ መብቶች ተግባር ላይ ይውሉ ዘንድ ነው "የዴሞክራሲ መብት ያለገደብ!" አታጋይ መፈክር የሆነው። በየጊዜው በተነሱ እንቅስቃሴዎች ያለአግባብ የታሠሩ ይፈቱ ዘንድ "የፖለቲካ እስረኞች ይፈቱ!" እየተጮኸ አንዱ ሲፈታ ሌላው የሚታሰረው። የሃይማኖት አድልዎ፣ የሴቶች የበታችነት በመንሰራፋቱ ነው "የሃይማኖት እኩልነት፣ የሴቶች እኩልነት" በእስልምና ወገኖችና በሴት እህቶቻችን አጀቢነት አደባባይ የወጡት። የርዕዮቱ አመጣጥ ሀገር ቀርሶ ቢሄድም የብሔረሰቦች ጭቆና ነው "የብሔር ብሔረሰቦችን መብት እስከመገንጠል!" የወለደው።

የካቲት 1966 ሕዝባዊ እንቅስቃሴ እነሆ! 43 ዓመት አስቆጠረ። የአፄ ኃይለሥላሴን ዘመን አጃጅቶና አስረጅቶ፣ የደርግን ትውልድ መቅበር በፀፀት አስተክዞ፣ የኢሕአዴግን ዘረኝነት መጨረሻውን ግራ አጋብቶ እያንገዋለለ በመጓዝ ላይ ይገኛል። ሀገር ለልጆቿና ለሕዝቧ ትሆን ዘንድ ያኔ የጮኸ ትውልድ ዛሬ ወቅቱን በዓይነ ኅሊናው ይስለዋል።

*"አትነሳም ወይ. . .አትነሳም ወይ…ፋኖ ተሰማራ…ፋኖ ተሰማራ…ተው ስማኝ ሀገሬ…ኸረ ስማኝ ሀገሬ"*

ተሰልፎ ለጮኸባቸው ጭልጥ አርገው ይነጉዳሉ። ከስድስት ኪሎ ቀዳማዊ ኃይለሥላሴ ዩኒቨርስቲ በአምስት ኪሎ ቁልቁል አንደርድረው አራት ኪሎ አድርሰው ብረት ቆብ ሄልሜት ካጠለቁና መመከቻ ጋሻና ቆመጥ ዱላ ከያዙ "አድማ በታኝ" "ፈጥኖ ደራሽ" ፖሊሶች ጋር ያላትማሉ። የወዳደቁ ወጣቶችን ስለው ወደ ጣቢያና ሆስፒታል አሻግረው ትዝታ ብቻ ሆነው ቀርተዋል። ድል አልባ ትዝታ። ያልተሰማ ጩኸት። ድምጽ አልባ ጩኸት። ሀገር ለገዳይ የሆነችበት ጩኸት። መሬት ለመንግሥት የሆነበት ጩኸት። መብት ለደርግ ጠባቂዎች የተሰጠበት ጩኸት። ኢትዮጵያዊነትን እምሽክ አድርጎ የበላ ጩኸት። ጀግንነትን በፍርሃት የለወጠ ጩኸት። ኢትዮጵያዊ ኩራትን ለባዕድ አምልኮ ያስረከበ ጩኸት። ፋሺዝምን አንግሶ ለዘረኝነት ያስረከበ ጩኸት። ሀገርን ቀርሶ የዘር ክልልና ግለኝነትን ያነገሰ፣ አኩሪ ባህልን ለመጤ ያስረከበ፣ ሰንደቅ ዓላማን ጨርቅ ያሰኘ፣ ታሪካዊ ቅርሶችን ድንጋይ ያስባለ በትውልዱ ላይ ጥቁር ነጥብ የጣለ ጩኸት። የሀገር ያለህ! የሕዝብ ያለህ! ያሰኘ ጩኸት።

የየካቲት 66 ሕዝባዊ አብዮት መሪ ኮከቡን ባለማግኘቱ የወታደሩ ክፍል እራሱን አሰባስቦና አደራጅቶ ከአስተባባሪ ኮሚቴነት ወደ ወታደራዊ አስተዳደር ደርግነት በጊዜያዊነት ስም ተሸጋገረ። ደርግ የካቲት 1966 ሕዝባዊ እንቅስቃሴ ተገን በማድረግ እስከ ሰኔ 21 ቀን 1966 ዓ.ም. ድረስ ሕጋዊ ሽፋን ሳይኖረውና ለንጉሡ ታማኝ አገልጋይነቱን በመግለጽ የቀድሞ መሳፍንትትንና መኳንንትን እንዲሁም ከፍተኛ ወታደራዊ ሹማምንቶችን "እጃቸውን እንዲሰጡ" በማግባባት ዘለቀ። በቀጣይነትም ይህ ወታደራዊ ስብስብ "የጦር ኃይሎች የፖሊስ ሠራዊትና የብሔራዊ ጦር አስተባባሪ ደርግ" በማለት ሰኔ 21 ቀን 1966 ዓ.ም. እራሱን ለሕዝብ ይፋ አወጀ። ወደ መንግሥት ለውጥ የሚወስደው መሸጋገሪያ ድልድይ ተጀመረ። "ሕዝባዊ አብዮቱን ግብ ሊያደርስ የተደራጀ ኃይል ባለመኖሩ የወታደሩ ኃይል እንቅስቃሴውን መምራት ግድ ነው" ያሉ ምሁራንም ደርግን ከበብ በማድረግ አማካሪ ሆኑ።

ደርግ በቀጣይ ሁለት ወራት የንጉሱን ዋና ዋና መዋቅራዊ ዘርፎች በመቆጣጠርና በደርጉ መዋቅር በመጠቅለል መስከረም 2 ቀን 1967 ዓ.ም. በአዋጅ ንጉሡን ከሥልጣን አውርዶ፣ ሕገ መንግሥቱን ሽሮ፣ ምክር ቤቱን በትኖ ሥልጣኑን በጊዜያዊ አስተዳደር ስም ተቆጣጠረ። ደርግ ሥልጣኑን እንደያዘ ከአወጣው አዋጅ ጋር ያስተላለፈው የዴሞክራሲ ማዕቀብ የወቅቱን ተራማጅና ሀገር ወዳድ የኅብረተሰብ ክፍል ለጥያቄ ጋበዘው። የወታደራዊው አገዛዝ አካሄድንና አዝማሚያ ቆም ብሎ ይቃኝ ዘንድ ፍንጭ ሰጠው።

ደርግ ንጉሡን ከሥልጣን ያወረደበትና "በኢትዮጵያ ትቅደም" ስም የመጀመሪያው መብት እገዳ አዋጅ በ"ፍፁም ነው እምነቴ" መጽሐፍ እንዲህ ይነበባል፦

*"ዛሬ መስከረም ሁለት ቀን 1967 ዓ.ም. ጀምሮ ቀዳማዊ ኃ/ሥላሴ ከሥልጣናቸው ወርደዋል። ሕዝቡም ጊዜያዊ እንደራሴዎቹን መርጦ ሕገ መንግስቱ እስኪታወጅና መንግስት እስኪቋቋም ድረስ ወታደራዊው ደርግ የመንግሥቱን ሥልጣን ይዞ ሀገሪቱን ይመራል..."*

*"ይህ አዋጅ እስከጸናበት ጊዜ ድረስ 'ኢትዮጵያ ትቅደም' የሚለውን ዓላማ የመቃወም አድማ የሚያደርግ፣ ሥራ የሚያቆም፣ ያለፈቃድ ሰላማዊ ሰልፍና ስብሰባ የማድረግ በጠቅላላው የሕዝቡን ፀጥታና ሰላም የሚነሳ ተግባር መፈጸም ክልክል ነው።"*

ከዚህ አዋጅ በኋላ እጃቸውን መስጠት ፈቃደኛ ያልሆኑ የንጉሡ መኳንንት፣ ባላባትና ወታደራዊ ሹማምንት ተደመሰሱ፣ እርምጃ ተወሰደባቸው ዜና

*". . .የፍየል ወጠጤ*
*ትከሻው ያበጠ ልቡ ያበጠበት*
*እንዋጋ ብሎ ከነብር ላከበት፤*
*የማትረባ ፍየል ዘጠኝ ትወልዳለች*
*ልጆቿም ያልቃሉ እሷም ትሞታለች።. . ."*

የሚለው የይርጋ ዱባለ ዜማ በወታደራዊ ማርሽ እየታጀበ መለፈፍ የየዕለት ተግባር ሆነ። በዚህም ሽፋን ከንጉሡ የስልጣን እርከን ጋር ምንም ግንኙነት የሌላቸው በ"ወንበዴ" እና በ"ሽፍታ" ስም እየተደባለቁ ተረሸኑ።

"ደርግ ሕዝባዊ አብዮቱን በጊዜያዊነት ይዞ እውን ሥልጣኑን ለሕዝብ አስረክቦ ወደ ወታደራዊ ካምፑ ይመለሳልን?" የሚለውን ጥርጣሬ ከጅምሩ ተቀብለው "ሂሳዊ ድጋፍ" እንስጠው ያሉትን ኩምሽሽ ያደረገበትና በጥቅሉ ደርግ ሕዝባዊ አብዮቱን የበላበት ወርና ቀን ኅዳር 14 ቀን 1967 ዓ.ም. ነበር። የደርጉን ሊቀ መንበር ብርጋዴር ጄኔራል አማን አንዶምን ጨምሮ የቀድሞ የንጉሡ ባለሥልጣናትና ሁለት የበታች ሹሞችን በጠቅላላ 60 ባለሥልጣናትን ያለምንም ፍርድ በአንድ ምሽት በመረሸን የቀበረው ደርግ በተራ ቁጥር 61 የየካቲትን ሕዝባዊ አብዮት ቀብሮታል። "ያለምንም ደም" የተዘመረለትን አብዮት "ይደመሰሳሉ፣ ይወድማሉ" መሰል ቃላት ተኩት። ሕዝባዊ አብዮት አከተመ ! ደርግ ወደ አንድ አምባገነን ፈላጭ ቆራጭ አገዛዝ እንደሚያመራ ፍንጭ ሰጠ። ይህም በሁለት ዓመት ውስጥ ዳግማዊ የደርግ ሊቀ መንበሩን ብ/ጄ ተፈሪ ባንቴንና ሌሎች የደርግ አባላትን እረሽኖ ሌ/ኮ አጥናፉ አባተን አንቆ ተግባራዊ ሆነ። ደርግ የሚባልን ስብስብ ንዶና አዳክሞ አጃቢ ምሁራንንም አጣጥሞ "ከቆራጡ መሪ ጋር ወደፊት" ሲያስፎክር "የቆራጡ መሪ ፍሬው ጎመራን" አዘመረ። መሪ ኮከቡን ያጣው የካቲት 66 ሕዝባዊ አብዮት አምባገነን ሥርዓትን ወለደ።

ሕዝባዊ አብዮቱ ከ120 የደርግ አባላት ስብስብ "የጋራ አመራር" ደም በደም እየተሸጋገረ ወደ አንድ አምባገነን ፋሽስት መንግሥቱ ኃይለማርያም ፈላጭ ቆራጭ የ"ደም አብዮት" ተሸጋገረ። አብዮቱ ከሕዝባዊነት ወደ ደርግነት ብሎም ወደ አንድ ግለሰብ አመራር በደርግና ከባቢዎቹ አባባል "ወደ አጥቂነት ተሸጋገረ"። ኅዳር 14 ቀን 1967 ዓ.ም. በግፍ ደም ሕዝባዊ አብዮቱ አቅጣጫውን ሳተ፣ እንደ ኢሕአፓ አባባል "ጭፍን ፋሺዝም በኢትዮጵያ ነገሠ"።

"ፍለጠው፣ ቁረጠው" "ይደመሰሳሉ፣ ይወድማሉ" መፈክሮች ለሻለቃ ሲሳይ ሀብቴ፣ ለሻምበል ኪሮስ ዓለማየሁ፣ ለኮ/ል ጌታቸው ናደው መሰል ደርግ አባላት ሳይሳሱ እየጠራረገና እየደመሰሰ በቀጣይነት የሕዝብ ልጆችንና ሀገርን ጨረሰ። "ዘመቻ መንጥር"፣ "ዘመቻ ደምስስ" ከቤት ለቤት አሰሳ ወደ "ነፃ እርምጃ" ተሸጋገሩ። ይህም አልገድብ ብሏቸው ወጣቶች፣ ጎልማሳዎችንና ተማሪዎችን ማዕከል ያደረገ ሕፃናትን፣ አባትንና እናትን አለይ ያለ የደርግ "ቀይ ሽብር" ትውልድ ጨርሶ የግድያው መደምደሚያ የራሱን ጄኔራሎች አድርጎ 17 ዓመት በደም ሰክሮ፣ በደም አጓርቶ ሀገርን አስገንጥሎና ለዘረኛ አገዛዝ አስረክቦ የፈረጠጠው ደርግ የየካቲት 66 ሕዝባዊ አብዮትን ተገን አድርጎ ኢትዮጵያ ምንጊዜም ልትተካቸው የማትችለውን አበባዎቿን ቀጥፎ አሸልቧል።

«ያ ትውልድ ተቋም» የየካቲት 1966 ዓ.ም. ግብታዊ አብዮትን ስናስታውስ ለመብትና ነፃነት፣ ለዜግነት መብት፣ ለሀገር አንድነትና ሉዓላዊነት፣ ለሕዝብ መንግሥት እውን መሆን፣ ሀገር የልጆቿ ትሆን ዘንድ የተጮኸውና የፈሰሰው ደም እንዴትና? ለምን? አቅጣጫውን ሳተ የሚለውን ዘርዝረን ባንገባበትም በመጠኑም ቢሆን አካሄዱን በመቃኘት ነው። ዳር እስከዳር የኢትዮጵያ ሕዝብ የተሳተፈበት የካቲት 66 ሕዝባዊ አብዮት መሪ ኮከቡን ማጣት ወዴት ሊያመራ እንደሚችል የካቲት 66 ትምህርት ይሆን ዘንድ በመጠቆም ነው። መሪ የሌለው ሕዝባዊ እንቅስቃሴ የተነሱ ሀገራዊ ጥያቄዎችን አይፈታም የሚል ድምዳሜ ውስጥ ባይገባም የዛሬ 43 ዓመቱ የካቲት አብዮት በተግባር የታየ ትምህርት ቤት መሆኑን ለመጠቆም እንወዳለን።

ለሀገርና ለሕዝብ መብትና ነፃነት ግምባር ቀደም በመሆን መስዋዕትነትን የከፈላችሁ ብርቅዬ የኢትዮጵያ ልጆች ምን ጊዜም አንረሳችሁም። ለሀገርና ሕዝብ ያፈሰሳችሁትን ደም የከሰከሳችሁትን አጥንት ፋሽስት ተዝናንቶበት፣ ዘረኝነት በቅሎበት፣ የአኩሪ ታሪካችን ጥላሸት ቀቢዎች ቢበራከቱም ጊዜ የናንተ ትሆናለች እንላለን። የፈሰሰው ደም የተከሰከሰው አጥንት ትንሳዬ ለኢትዮጵያ እንደሚሆናት ተስፋ አለን። ኢትዮጵያና ትውልድ ታሪካችሁን ክፍ ያደርጉታል ስንል ከ«ያ ትውልድ ተቋም» ክብር ለእናንተ፣ ክብር ለሰማዕታት፣ ኢትዮጵያችን ለዘላለም ትኑር! እንላለን።

**ክብር ለኢትዮጵያና ለሕዝቧ!!!**
**«ያ ትውልድ ተቋም»**
**የካቲት ፲፮ ቀን ፪ ሺህ ፱ ዓ.ም. (February 23, 2017)**

ዋቢ ማጣቀሻ፡

- ነሲቡ ስብሐት፡ "ፍፁም ነው እምነቴ" ቀይ ሽብር የከፍተኛ 15 እውነተኛ ታሪክ፤ መስከረም 2007 ዓ.ም. ሰሜን አሜሪካ።
- ዕለታዊው የአዲስ ዘመን ጋዜጣ
- የኢሕአፓ ልሳን፤ ዴሞክራሲያ ቅጽ 1 ቁጥር 17 ኅዳር 15 ቀን 1967 ዓ.ም. "ጭፍን ፋሺዝም በኢትዮጵያ ነገሠ"። (http://yatewlid.com/index_htm_files/Demo_Vol_1_No_17_Hidar15_1967.pdf)

ድረ ገጽ ፦ www.yatewlid.com, www.yatewlid.org
ኢሜል ፦ yatewlid@gmail.com, yatewlid@yahoo.com
ምስለ ገጽ ፦ YaTewlid